# ከኢትዮጵያን ሰማይ ድረገጽ አዘጋጅ የተሰጠ ጊዜያዊ ማሳሰቢያ

## <u>ጌታቸው ረዳ (*Ethiopian Semay*)</u>

### <u>*ውድ የ Ethiopian Semay ድረገጽ ተከታታዮች ሆይ!*</u>

ሕዝብ ውስጥ ላለፉት 27 አመት ወያኔን ስታገል መቆየቴ ይተወቃል። ወደ 5 ሚሊዮን የሚሆን የትግራይ ማሕበረሰብ ውስጥ እኔ እና ገብረመድህን አርአያ እንዲሁም አቶ አብርሃም ያየህ ወያኔን በመቃወም በግምባር ቀደም ወጥተን የተጋፈጥን ብቸኛ ትግሬዎች መሆናችን ታሪክ የዘገበው ሃቅ ነው። እኔ በግሌ 5 የአማርኛ እና አንድ የትግርኛ መጽሐፍቶችን ባለፉት 27 አመት ለዚህ አስቸጋሪ ትግል አበርክቼአለሁ።

ከ80 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ሕዝብ ውስጥ በጣም ጥቂት ተቃዋሚ በነበረበት ወቅት በግምባር ቀደም አደባባይ ወጥቼ አገር ውስጥ በሚታተሙ በጋዜጦች፤መጽሔቶች እንዲሁም ድረገጾች ላይ ከፍተኛ የሆነ የቅስቀሳ ትግል በማካሄድ ከወያኔ ፤ከኦሮሞ የጥላቻ ቡድኖች እንዲሁም ከሻዕቢያ የጥላቻ ቡድኖች፤ ሌላ ቀርቶ “ከታቃወሚ ተብየው” ጋርም እልህ አስጨራሽ ትግል በማካሄድ ታሪክ የዘገበው ትግል አካሂጃለሁ።

ዛሬ የውጭ ሃይሎች እና በውስጥ ሃይሎች በሚመሩት “አፍዝ ወ አደንዝዝ የጥገና ለውጥ” (ሂፕኖቲክ) የመደመር ፍልስፍና “ኢትዮጵያ ወዴት እንደምታመራ በእርግጠኛነት የሚያውቅ ፖለቲከኛም ሆነ ተራ ዜጋ የለም”። ሰሞኑን ግንቦት 7 የተባለ ጸረ አማራ እና ጸረ ኢትዮጵያ ቡድን አዲስ አበባ ገብቶ የተደረገለት አቀባበል ስመለከት (ያውም 15 የሚያክሉ ቦዲ ጋርዶች) እንዲሁም በስሜት በሚጨፍር ያልተገራ የአዲስ አበባ ወጣት ለግንቦት ሰባት መሪዎች እና ለመሳሰሉ አጭበርባሪዎች ባሳየው ክብር እጅግ አዝኛለሁ።

እስከዚህ ድረስ ትግሉን ገፍቻለሁ። ኢትዮጵያውያን (ከተሜው) ነብሰገዳዩን፤ዋሾውን፤አጭበርባሪውን ፤ገንጣዩን ሁሉ እየጨፈረ የሚቀበል፤እግር የሚስም፤ገንዘብ የሚለግስ፤መኪና የሚሸልም ከሆነ የኔ ትግል ፍሬው ድካም የሚሆን ከሆነ እና ሕዝቡ በስሜት ከመነዳት ነጻ የማይወጣ ከሆነ “ለምን እንደምጮህለት ጥያቄ ውስጥ ስለገባ”፤ **<u>ከዚህ ቀን ጀምሮ ላልተወሰነ ጊዜ ትግሌን አቁሜአሁ።</u>** ካሁን ወዲህ በስሜት እየጨፈረ ያለው ኢትዮጵያዊ “ቢፈርስ፤ቢረገጥ፤ቢሰደድ፤ ቢታሰር፤ቢንገላታ” እራሱ የጋበዘው ችግር ስለሚሆን የማዝንለት አይሆንም። መንጋው ሕዝብ ዕጣ ፈንታው በትዝብት ቆሜ እንድመለከተው ለተወሰ ጊዜ ወስኛለሁ። ይህንን በሚመለከት ሰፊ ማብራሪያ ስለምሰጥ ላሁኑ ግን በዚህ ላቁም። መልካም መደመር!መልካም ነፃነት! መልካም ዕድል!

ጌታቸው ረዳ (Ethiopian Semay ድረገጽ አዘጋጅ) getchre@aol.com